# የኢሳት አስጊና አደገኛ አቅጣጫ

ከዶክተር ጌታነህ

ኢሳት ተፎካካሪ የሌለው ለዳያስፖራውና በሃገርም ውስጥ ላሉ ኢትዮጵያውያን መተንፈሻና መረጃ ነው ተብሎ የሚገመት በአብዛኛው በዳያስፖራው የሚደገፍ የሳተላይት መገናኛ ጣቢያ ነው። ተፎካካሪ የሌለው ስል እንቅስቃሴውን አስመልክቼ ሳይሆን እንደኢሳት ያለ ሌላ የመገናኛ (Midea) አገልግሎት በገበያ ላይ አለመኖሩንና ተጠቃሚው ወደደም ጠላም ከኢሳት ሌላ አማራጭ እንደሌለው ለማመልከት ነው። ኢሳት አቋዋሙንና በየትኛው ድርጅት ወይም ግለሰብ እንደተመሰረተ ብሎም የመጨረሻ አላማው ምን እንደሆነ በገንዘቡ ለሚረዳውና እምነት ለጣለበት ዳያስፖራና በኢትዮጵያ ውስጥ ላለው ወገን ለመግለፅ አሻፈረኝ ብሎ ቆይቶአል። በቅርቡ ደግሞ የህዝቡን ፈቃድ ሳይጠይቅና ሳይናገር የኢትዮጵያን ቀንደኛ ጠላት ኢሳያስ አፈወርቂን ለመንብኘት ወደኤርትራ ጋዜጠኞቹን ከላከ በሁዋላ በአምባገነንነቱና በወያኔ ወዳጅነቱ የታወቀውን የኤርትራ መሪ የኢትዮጵያ አጋርና ወዳጅ ፣ የደሞክራሲ ምሳሌ አድርጎ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ እየለፈፈ ይገኛል። ይህንን አዲስና ያልተጠበቀ ተልእኮውን ዳያስፖራው ግራ የተጋባበት ቢሆንም በኢሳት ላይ በጣለው የጭፍና እምነት የኢሳትን ኤርትራ ድረስ ሄዶ ከኢሳያስ አፈወርቂ ጎን መሰለፍን በቁጣ ቃል ሲቃወም አልታየም አልተሰማም። ለነገሩ ኢሳት የተቃዋሚዎችን ድምፅ ማፈኑን የተካነበት በመሆኑ ወቃሾችም ቢኖሩ ከህዝቡ ጆሮ አርቆታል። ይልቁንም ሁሌ የምንሰማው ኢሳት የኢትዮጵያ ህዝብ “አይንና ጆሮ” የሚለውን ዝክር ነው።

የኢሳትን አገልግሎት ገና ከጅምሩ ከተከታተሉት ሰዎች አንዱ ነኝ። በመጀመሪያዎቹ ሁለት አመታት ኢሳት ከሰማይ የተላከ የነፃነት አጋር ብዬ በመቀበል አንዳንድ ጥያቄዎች በኖሩኝም የአእምሮዬን ደወል እያፈንኩ ኢሳትን ከመውቀስ ታግጄ ሁኔታውን በጥሞና መከታተልክ ጀመርኩ። የመጀመሪያው ጥያቄዬና የልቤ ከንካኝ የነበረው ለምን ኢሳት በደንቡ ህዝቡን ለትጥቅ እንዲነሳ አይገፋፋም? ለምን ለዘብተኛና ዳር ሆኖ አቸፍቻፊ አይነት አቋዋም ይይዛል የሚል ነበር። ኢሳት ልብን የሚኮረኩርና ቁጣን የሚያስነሳ (በጠላት ላይ) የሃገር ቁጭትን የሚቀሰቅስ ፕሮግራም አቅርቦ አያውቅም። ወሬ ያመጣልናል፣ ቃለ ምልልስ ያደርጋል፣ የወያኔን የየሳምንት ጭካኔና የህዝቡን ድምፅ ያሰማናል። ያ ሁሉ መልካም ነበር ዛሬም መልካም ነው። ነገር ግን ያ በቂ አልነበረምም አይደለምም። ዳያስፖራውም ከአመት አመት የወያኔን ጥፋት እየሰማ ብቻ መኖሩ በወያኔ ህልውና ላይ ምንም ለውጥ እንደማያመጣና ሃገራችንም በማነህ ማነህ ከአመት አመት ተስፋዋ እየደበዘዘ የወያኔ ጥፍርም በጥልቀት የሃገራችንን ማንቁርት እያነቀ መሄዱን ቀስ በቀስ የተረዳው ይመስላል። ለአንድ ህዝብ መደራጀትም ሆነ መንቀሳቀስ የመገናኛ ተቋዋማት አገልግሎትና አነሳሽነት (Agitation)

ትልቅ ሚና አለው። ዳያስፖራውም ሆነ በኢትዮጵያው ውስጥ የሚኖረው የወያኔ ሰለባ ኢሳት ያንን ሚና ይጫወታል ብሎ ነበር የጠበቀው። ለዚህም ነበር የላቡን ጥሪት ለድርጅቱ ሲያፈስ የከረመው ዛሬም የሚያፈሰው። ችግሩ የኢሳት ኣላማና የዳያስፖራው ፍላጎትና ከድርጅቱ የሚጠብቀው (Expectation) ስራ በጣም የተለያዩ ነገሮች እንደሆኑ አለማወቁ ነበር። ለምሳሌ በ "ከእርሶ ለእርሶ" ስልክ መልእክት የኢሳትን ስርጭት በኢትዮጵያ የሚከታተለው ህዝብ ስልክ እየደወለ በተደጋጋሚ ከሚጠይቃቸው ጥያቄዎች መሃከል ኣብዛኛዎቹ "እባካችሁ "ለሃገራችን ህይወታችንን ለመስጠትና ወያኔን ለመጋፈጥ ተዘጋጅተናልና ምሪት ስጡን" ፣ "ቀረርቱና ፉከራ አሰሙን" ፣ "አቅጣጫ ኣሳዩን" "ተነሱልን" የሚል ነው። በዳይስፖራውም መሃከል ከኢሳት አፈና አምልጠው የምንሰማቸው አስተያየቶች እንደሚያሳዩት ኢሳት ጠንካራ አቋዋም ይዞ ህዝቡ የሚታጠቅበትንና የሚዘምትበትን ጎዳና እንዲያመቻችና የትጥቅ ጥሪ ላላቸው ዝግጅቶች የበለጠ ጊዜ እንዲሰጥ አጥብቆ ይፈልጋል። የኢሳት ኣላማው ግን ያ አይደልም። ባለፉት ኣመታት በካናዳ ለኢሳት መዋጮና ለታማኝ ክብር በተደረገው ስብሳባ ላይ የኢሳት ከፍተኛ ባለስልጣን የሆነ ሰው ንግግር ሲያደርግ እግረ መንገዱን "ኢሳት ኢንፎርሜሽን ማቅረብ ብቻ ነው ግዴታው" የሚል አይነት ሃሳብ አቅርቦ ነበር። አባባሉ በደፈናው ጉዳት የሌለው ቢመስልም አጢኖ ላየው ግን የሚያሳስብ ጉዳይ ነው። ዳያስፖራው ኢሳትን ሲደግፍ ዋና ምኞቱ ሳተላይት ጣቢያው ኢንፎርሜሽን ከማቅረብም ባሻገር ህዝቡን እንዲቀሰቅስና ግፉ፣ ጋሻ ጦርህን አንሳ እያለ እንዲያበረታታው ብሎም እናት ሃገርን ነጻ ለማውጣት በሚደረገው ትግል ትልቅ ሚና እንዲጫወት ነው። ኢሳት ይህንን ሚና ለመጫወት ሃሞቱ እንደሌለው አልፎ አልፎ አድበስብሶ በጨረፍታ ከመጥቀስ በተቀር ህዝቡ ከድርጅቱ ተጨማሪና አክራሪ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን እንዳይጠብቅ በግልፅ አስታውቆ ኣያውቅም። ኢሳት ይህንን ካደረገ ደግሞ የገንዘቡ ምንጭ እንደሚደርቅ ያውቃል። ስለዚህም አድማጩን ህዝብ ውዥንብር ውስጥ ከቶ በማይከሰት ተስፋ ገንዘቡን እየለቀመ እድሜውን ማራዘምና ድርጅቱን ማስፋፋት መርጦአል። ጋዜጠኛ ወገን መያዝ የለበትም የሚለውን አባባል እንደ ምክንያት ለሚወስዱ የኢሳትን ሁኔታ አስመልክቶ ምን ማለት ይቻላል?። የኢሳት ገለልተኛነት የሚያስቀጣቸው አንደእኔ አይነቶች አንደሚሉት በዳያስፖራው ድጋፍ የሚንቀሳቀስ ማንኛውም ድርጅት የዳያስፖራውን ድምፅንና አቋዋም ሊያስተጋባ ግዴታው ነው። ስለዚህም ኢሳት ገለልተኛ (neutral) ኣቋዋም ሊኖረው ኣይችልም። ባጠቃላይ ኢሳት ትግሉ የፈጠረው ድምፅ ነው (ምናልባት ህዝቡ የማያውቀው ድብቅ አጀንዳ ከሌለው በቀር)። ሃገራችንን ኢትዮጵያን ከሕዋሃት ጭቆና ለማዳንና ዴሞክራሲያዊ ኣገዛዝን ለመመስረት በኣሁኑ ጊዜ ኣማራጭ የሌለውና ብቸኛው መንገድ የትጥቅ ትግል ነው። ይህም ጊዜ የማይሰጥ፣ አስቸኳዋይና ኣጣዳፊ ጉዳይ ነው። በህዝባችን ላይ እየተፈፀመ ያለው ገሃድ ምዝበራና እንግልት የመላው ኢትዮጵያውያንን ትኩረት ሊስብ ይገባዋል። ኣጥንትና ደማችንን መከስከሻችን ሰአቱ ኣሁን ነው። የትግላችን አቅጣጫ ቁጭ ብሎ ባዶ ተስፋን ከመጠበቅ ወደ አካላዊ እንቅስቃሴ መለወጥ አለበት። ለ

ከለዘብተኛ አቋዋሙ ባሻገር ኢሳት የኢትዮጵውያንን ትግል የሸረሸረበት ሌላው መንገድ የዳያስፖራውን ህልምና ኣላማ ወደራሱ አጀንዳ በመሳብ ነው። በየትኛውም የታማኝ በየነ መስተንግዶ ወይም የኢሳት ገንዘብ መዋጮ ከኢሳት ጋዜጠኞች (staff) መሃከል በኢትዮጵያ ስላሉት የትጥቅ ታጋዮችና ስለሚያስፈልጋቸው የሞራልና የቁሳቁስ አልያም የገንዘብ እርዳታ አንስቶ የህዝብን እርዳታ የጠየቀ ይለም ብል ማጋነን አይሆንም። ዳያስፖራው ታማኝ በየነን በየሄደብት እንደ አንድ ነፃ ኣውጭ ታጋይና መሪ አድርጎ ሲቀበለው ህዝቡ ለመሪና ታግሎ ለሚያታግል ቆራጥ ሰው ያለውን ጥማት ያሳየናል። ከዛም በላይ ዳያስፖራው  ከኢንፎርሜሽን ወደ ትጥቅ ትግል ለመሸጋገር እየተቁነጠነጠ እንደሆነ ይጠቁማል። ኢሳትና ታማኝ ግን ትኩረታቸው (ከተሳሳትኩ እታረማለሁ) የሳተላይቱን መገናኛ (ኢሳትን)ለማስፋፋትና ለማደራጀት እንጅ ከዛ ያለፈና ኮስተር ያለ አላማ ያላቸው አይመስልም። በሄዱበት ስለትግሉ ሳይሆን ስለኢሳት ብርቅዬነት የሚለፍፉት ጋዜጠቹና ታማኝ በየነም ራሱ ዳያስፖራው የኢሳትን ከበሮ እየደለቀ እንዲኖር ኣደንዝዘውታል። በየስቴቱ ኣመት በቀየረ ቁጥር የሚደረገው ዝግጅት ለኢሳት ዳጎስ ያለገንዘብ ማሰባሰቢያ እንጅ ስለትግሉ አይደለም። ሳያውቀው ዳያስፖራው በኢሳት አዚም ፈዞአል። የሚገሳውና የሚፈሳው ሁሉ ስለኢሳት ነው። ምነው ታጋዮችን እናስታጥቅ፣ ትጥቅና ስንቅ እንላክ፣ ገንዘብ እንሰብስብ? የሚል እንቅስቃሴ ከታማኝና ከኢሳት አይሰማም? ሁልጊዜ ለኢሳት ነው ሩጫው። ኢሳት ነፃ ያወጣን ይመስል? እውነትም ዛሬ የኢሳትን የፐሮግራም አይነቶች ብንመረምር ድርጅቱ ገንዘብና ጊዜ እንደተትረፈረፈው ያሳየናል። ኢሳት በቴሌፎን፣ የኢሳት ተምቦላ፣ ኢሳት በአምስተርዳም፣ ወዘተ ወዘተ። ጋዜጠኞቹና አስተዳደሩም ለራሳቸው ጥሩ የስራ መስክ ከፍተው ተደላድለው ኑሮን በአሜሪካ እየቀጩት ነው። በተለይ ዛሬ ዛሬ የኢሳትን ፕሮግራም የሚከታተሉ እንደሚመሰክሩት የኢሳት ገንዘብ መዋጮ ዜና አሁንም አሁንም መስማቱ ትእግስታቸውን እየተፈታተነ ነው። የሰው ሞት ለሬሳ ሳጥን ሰሪ ደስታ ነው እንዲሉ የኢትዮጵያ ችግር እየረዘመ መሄድ እንደኢሳት ላሉ ድርጅቶች መንሰራፋት ምክንያት ሆኖአል። ጥያቄው ይህ በዚህ ደረጃ እስከመች ነው የሚቀጥለው? የሚለው ነው። ዳያስፖራውም ለኢሳት የኪሱን ገንዘብ እያራገፈ ፤ ኢሳትም ባዶ ወሬውን እየነዛና የህዝቡን የተወጠረ የመስዋእትነት ወኔ በኣጉል  የወሬ ቱልቱላ እያኮላሸ በዚሁ “ባለህበት ሂድ” እስከመቼ ነው የምንቀጥለው? ኢሳት ዜና እያነበበ ፣ ኢንተርቪው እያደረገ ፣ አንዳንዴም ሰበር ዜና እያለ፣ የሚሰጠው አገልግሎት ለዳያስፖራውም ሆነ ለጭቁኑ የኢትዮጵያ ህዝብ በቂው ነው ወይ? የዳያስፖራው ኢሳትንና መደገፍ መጨረሻ ፋይዳው ምንድነው? የሃገራችንን አሰቃቂ ሁኔታ አይተን ሰምተን ጠግበናል። አሁን ለመፍትሄ የመታገያችን ጊዜ ነው። ኢሳትና ታማኝም ቀረርቶና ቅስቀሳ ፕሮግራማቸው ውስጥ የሚያካትቱበት ጊዜ አሁን ነው። አለበለዛ ወሬ ጠግበናል። ወሬ ብቻውን ወሬ ነው።

ሌላው ኢሳትን በተመለከተ የታዘብኩት ነገር አልፎ አልፎ የሚቀርቡ ኢትዮጵያውያን ህዝብ የሚያስቆጡ እንግዶች ናቸው። በህዝቡ ላይ ንቀት የሚያሳዩ ፕሮግራሞች ብዬ የምላቸው በመድረኩ ሊቀርቡና ሊስተናገዱ የማይገባቸው ግለሰቦች ኣንዳንዴም

የህዝብ ጠላቶች በኢሳት መድረክ በታላቅ ከበሬታ ሲስተናገዱ ይታያሉ። እንዳልኩት ኢሳት የህዝቡ ፈቃድ ተገዢ መሆን ግዴታው ነውና የህዝቡን ጠላት ማስተናገድ ብልግና ነው። ከበስተሁዋላው የሚነዳው ድብቅ ሹፌር ከሌለው በተቀር!! ምናልባት ብርሃኑ ነጋ?

ኢሳቶች ፕሮግራማቸውን ያደምቃል ብለው ይሰቡትን ማንንም ሰው ግለሰቡ በፕሮግራማቸው ለመገኘት ፈቃደኛ እስከሆነ ድረስ ትከሻቸው ላይ እንኮኮ ይሉታል። የጋበዙት ሰው በኢትይዮጵያ ህዝብ ላይ ምን ጥቃት አድርሶኣል?፣ ምን ኣይነት ታሪክ ያለው ሰው ነው? ብለው ኣይጠይቁም እነሱ የሚጠይቁት ወሬ ያደምቅልናል ወይ? ብቻ ነው። እንደነስብሃት ነጋ ያሉትን ሃገር የሸጡ ሽፍቶች “ አንጋፋው የህዋሃት ታጋይ” እያሉ ማቆላመጥ ሊያበቃ ይገባዋል። የኢትዮጵያን ህልውና የሚክዱና ግዛቱዋንም ለባእድ ኣሳልፈው የሰጡ እንደነስብሃት ነጋና እንደመለስ ዜናዊ አይነቶች “አንቱታም አይገባቸውም።” ኢሳት ከሁሉም ጋር ለመወዳጀት የሚጫወተው ጨዋታ (playing nice) ፍፁም ሊወገድ ይገባል። ትዝ ከሚሉኝ የኢሳት ግብስብሶች መሃከል እነ ጃዋር መሃመድ፣እነአረጋዊ በረሄ፣ አባ መላና ኤርሚያስ ለገሰ የመሳሰሉት ይገኙበታል። አረጋዊ በረሄ የታላቁዋን ትግራይ ምስረታና የኣማራውን ጭፍጭፋና ፕላን የነደፈ ዋና የደደቢት መሪ ሆኖ ሳለ ኢሳቶች ምንም ሳይገዳቸው የመድረካቸው ተጠቃሚ አድርገውታል። በአቋዋም መለዋወጡ ዝነኛ የሆነው ኣባ መላም ከትግራዩ መንግስት ጋር ሲሞዳሞድ ቆይቶ እንዲሁ ኣንድ ጠዋት ደግሞ ወያኔን እቃወማለሁ በማለቱ ኢሳቶች ተሩዋሩጠው ዙፋናቸው ላይ ቂጢጥ አደረጉት። ኣባ መላ ዛሬም ድረስ መላው ኣልታወቀም። ጃዋር መሃመድን መሳይ መኮንን “ወጣቱ የፖሊቲካ ምሁር” እያለ ሲያዘባንነው የነበር ሰው ዛሬ ኦሮሞ ኣንደኛ እያለ ህዝብ የሚከፋፍል ከሃዲ ሆኖአል። የቅርብ ጊዜው ኮከብ ተጨዋች ደግሞ ኤርሚያስ ለገሰ የተባለ አፈ ጮማ ከወያኔ ጋር ሆኖ የኢትዮጵያን ህዝብ ሲቦጠቡጥና ሲዘርፍ ከርሞ ወደኣሜሪካ ሲማጣ ለኢሳቶች ኢንተርቪው ለመስጠት ፈቃደኛ በመሆኑ ኢሳቶች ኣሜን ብለው ተቀበሉት። ዛሬ ኣቶ ኤርሚያስ ለገሰ የኢሳት ዋና ሃሳብ ሰጪ ቁንጮ ሰው ሆኖአል። እዚህም መጥቶ ለኢሳት የሰጠው ፉሩሽካ የኣሮጊቶች ወሬ ምንም ኣዲስ ነገር ያልገለጠ ያው ለኣመታት ህዝቡ ያወቀውን ሰቆቃ ነበር። እሱ ግን ኢሳትን በከፍተኛ ደረጃ ተጠቅሞበታል። ትዝ ይለን እንደሆነ ይህው ወንጀለኛ የፃፈውን መፅሃፍ ኢሳቶች ነበሩ እንደጉድ ያስተዋወቁለት። በዲያስፖራው ገንዘብ የተዋቀረውን የኢሳትን መድረክ አቶ ኤርሚያስ ለገስ በሚገባ ወደ ብር መንዝሮታል።

እነኝህ ከላይ የተጠቀሱት የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች በኢሳት መድረክ መቅረብ ካለባቸው ደግሞ ኢሳት ስለቀድሞው ተግባራቸው ጠካራ ጥያቄ እየጠየቀ ሃጢኣታቸውን ማናዘዝና ህዝቡንም ይቅርታ እንዲጠይቁ ማስማማት ነበረበት። ያለበለዛ ግን የኢትዮጵያን ህዝብ ከወያኔ ጋር ኣብረው ሲጫወቱበት ቆይተው ኣሁን በተለያዩ ምክንያቶችህ አገር ለቀው ሲወጡ ኢሳት መድረክ ላይ ወጥተው ራሳቸውን ከወንጀል ነፃ እንደሆኑ ኣድርገው ከነእድፋቸው በህዝቡ ፊት እንዲዋሹና እንዲመፃደቁ

ማድረግ ህዝብን መናቅ ነው። ኢሳትም ለኢትዮጵያ ህዝብ አክብሮት እንደሌለው የሚያሳይ ነው። እነኝህ ሰዎች በሰጡት ኢንተርቪው እንዳየነው አንድም የማናውቀውን ሚስጥር የገለጡት የለም። ምን ፈፅመሃል? ምን ሚና ተጫውተሃል በጭቆናው ውስጥ? ተብለው አልተጠቁም። ያ ደግሞ የሚያሳፍር ነው።

## የኢሳት ማስክ (ሽፋን) ተገፈፈ

## የባሰ አታምጣ

ኢሳት ከመጀመሪያውም ኣመሰራረቱንና ኣቁዋሙን ግልፅ ሳያደርግ ነበር የመጣው። በአንድ ወቅት ከኣድማጮቹ መሃከል ኣንዳንዶች የኢሳትንና የግንቦት ሰባትን ግንኙነት ኣስመልክቶ ጥያቄዎችን መጠየቅ ጀምረው ነበር። ነገር ግን ድርጅቱ ባለው ፑልፒት (መድረክ)ሃይልና በአንዳንድ ታዋቂ ደጋፊዎቹ ኣማካኝነት ጠያቂዎቹንና ጥያቄዎቻቸውን ለማፈን ችሎኣል። ኢሳት ነፃ መድረክ ነው ሁሉንም ያስተናግዳል ቢባልም መድረኩን እንደግል ንብረታቸው ኣድርገው ቤተኛ የሆኑበት እንደ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ያሉ ሰዎች ከድርጅቱ ጋር ምን ኣይነት ግንኙነት ቢኖራቸው ይሆን እንዲህ ገቢና ወጭ ሊሆኑ የቻሉት ያሰኛል። በኣንፃሩ ደግሞ በኢትዮዮጵያ ውስጥ ስላለው ሁኔታ አበጥረው የሚያውቁ ኣንዳንድ ምሁራን ከመድረኩ ተገልለው ይገኛሉ። ስለዚህም ነበር ዳያስፖራው ኢሳት የብርሃኑ ነጋ እምቢልታ ነፊ ነው ወይ ብሎ በተደጋጋሚ ጥያቄ ያቀረበው። ኢሳት ግን በጉዳዩ መልስ ከመስጠት ፋንታ ኣሻፈረኝ ብሎ እስከዛሬም ድረስ ኣድማጩን ህዝብ እንቆቅልሽ ውስጥ ከቶታል። የኢትዮጵያ ህዝብ በውጭም ሆነ በሃገር ውስጥ ያለው በገንዘቡና በጉልበቱ የሚረዳው ኢሳት በማ ኣዛዥነትና ምሪት እንደሚንቀሳቀስ ማወቅ መብቱ ነው። ይህም በጣም ኣስፈላጊ ነው።

በዛም ሆነ በዚህ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ኢሳትን መከታተሌን ሳላቁዋርጥ ኮፒዩተሬን ቢያንስ በየሁለት ቀኑ ወደ ዌብ ሳይቱ መደገኔን ኣልትውኩም ነበር። የቆረጠልኝ ፋሲል የኔ ኣለምና መሳይ መኮንን ኤርትራ ከገቡ በሁዋላ ነበር። በእውነት የማይታመን ክህደት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የፈፀሙት ያኔ ነበር ብል ማጋነን አይሆንብኛም። የጋዜጠኞቹ ከአምባገነኑ ኢሳያስ ጋር መገናኘት ብቻ ሳይሆን ለኢሳያስ አለትላች ውሾች መሆናቸው ነበር ሁላችንንም ያሸማቀቀን። የእነ መሳይ መኮንን ወደ ኤርትራ መሄድ ግን የገለፀው አንድ ትልቅ ሚስጥር ቢኖር ድርጅቱ የማነው የሚለውን ሚስጥር ነው። በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ ኢሳት በግንቦት 7 ባለቤትነትና ምናልባትም በኢሳያስ የእጅ አዙር ቁጥጥር ስር እንዳለ ዛሬ ግልፅ ሆኖአል። ከጋዜጠኞቹ የኤርትራ ጉዞ በፊት ኢሳት ከተመሰረተበት ጊዜ ኣንስቶ ብርሃኑ ነጋ ና ኣንዳርጋቸው ፅጌ በኤርትራ ውስጥ ሆኖ ስለመዋጋት ኣስፈላጊነት ደጋግመው ሲሰብኩን እንደነበር እናውቃለን። ሃሳቡን ኣብዛኛው ዳያስፖራ ሊውጠው ባለማቻሉ ስር ሳይሰድ እንደተድበሰበሰ ቀርቶ ነበር።

የእነ ፋሲል የኤርትራ ጉዞ በእኔ ግምት ሁለት ተልእኮ ነበረው። ኣንደኛ ኤርትራ ሄደው የቪዲዮና የኢንተርቪው መረጃ ይዞ መምጣትና ያንን ሳቢያ በማድረግ የተለመደውን የዳያስፖራውን ኪስ ለመበዝበዝና የግንቦት ሰባትን ኣባላት ማሳደግ ሲሆን። ሁለተኛው ደግሞ የብርሃኑ ነጋን የወደፊት የስልጣን ህልም ገሃድ ለማድረግ ኣንድ ደረጃ ወደፊት ማራመድ ነበር። ይህንንም የምናውቀው ከጋዜጠኞቹ ጉዛ ሁዋላ ወዲያው የሰማነው ነገር የብርሃኑ ነጋን መሾም እንደነበር ስናይ ነው። ማ እንደመረጠው ምርጫውም መቼ እንደተካሄደ ማንም ሳያውቅ ብርሃኑ ነጋ "የኣርበኞች/ግንቦት ሰባት" ጣምራ ግንባር ሊቀመንበር ተብሎ በኢሳት መተዋወቅ ጀመረ። ስለምርጫው የሰማና ያየ ሰው ካለ ይጠቁመኝ እኔ ግን ኣሳየሁም። ምናልባትም ይህ የብርሃኑ ነጋ ሊቀመንበርነት በአለቃቸው በኢሳያስ ኣፈወርቂ የተሰጠው ይሆናል ብዬ ኣምናለሁ። ከተሳሳትኩም እታረማለሁ።

መሳይና ፋሲል ከኤርትራ ይዘው የመጡት የቪዲዮና የኢንተርቪው ጋጋታ የኢሳያስ አፈወርቂን፣ የግንቦት ሰባት ግንባርን፡ የአርበኞች ግንባርን እንዲሁም የትሕዴንን እውነተኛ ኣቋዋም ያሳያል ብሎ የሚያምን ሰው ካለ ማሞ ቂሎ ብዬዋለሁ። ምክንያቱም የእነ ፋሲልና የመሳይ ኤርትራ ጉዞ ከዳያስፖራው ይደበቅ እንጅ ኢሳያስና ከላይ የጠቀስኩዋቸው በኤርትራ የተቀመጡ ግንባሮች ኣስቀድመው ያወቁትና የተዘጋጁበት ጉዳይ ነው። ያም ማለት ኢንስፔክተር ሲመጣ ሁሉም መልካም ጎኑን እንደሚያሳይና ጉድፉንም እንደሚያጠራ ሁሉ ኢሳያስና ተቃዋሚ ግንባሮቹ በሙሉ ተዘጋጅተው፣ የሚሉትን አጥንተው፣ ገላቸውን ታጥበው፣ ትጥቃቸውን አሳምረው፣ ዩኒፎርማቸውን ተኩሰውና ጥርሳቸውን ለፈገግታ ቦርሸው ነበር ጋዜጠኞቹን የጠበቁት። ያ ብቻ ሳይሆን ጉዞው ለረጅም ጊዜ የተቀመመና የራሱ የሆኑ ኣጀንዳዎችም ስለነበረው በኤርትራ መንግስትና በኢሳት እንዲሁም በግንቦት ሰባት የተመከረና በቅደም ተከተል የተቀነባበረ እንደነበር ኣልጠራጠርም። ያም ማለት ፋሲል የኔአለምና መሳይ መኮንን ኢሳያስና ግንባሮቹ ተዘጋጅተውና ተወላውለው እንደሚጠብቁዋቸው ያውቁ ነበር። የሚያዩትና የሚሰሙትም ውሸት እንደነበር ያውቁም ነበር ብል መዋሸት አይሆንም። ለጥንስሱ ባይተዋሮች እኛ ጀሌዎቹ ብቻ ነበርን እንጅ።

መሳይና ፋሲል በኢሳያስ ፊት ቁጭ ብለው ኢንተርቪው ሲያደርጉት ልክ በዚህ በምእራቡ አለም ሴሌብሪቲዎችን ሲያዩ ነርቨስ እንደሚሆኑ ወጣቶች ነበር የደነዘዙት። በዛ ኣምባገነንና ወራዳ ሰው ፊት ተቀምጠው ድምፃቸው እየተንቀጠቀጠ ኣይናቸው ቁልጭ ቁልጭ ሲል ማየት ሽቅብ ሊያስመልሰኝ ምንም ኣልቀረውም ነበር። በጥያቄና መልሱ ወቅት መሳይ ኢሳያስን "ጤንነቶ እንዴት ነው?" ብሎ የጠየቀበትን ቪዲዮ ቴፕ እራሱ መሳይ ሲያይ ምን እንደሚሰማው እንጃ። እጅግ የሚያሳፍር ነበር። እኛ ኢትዮያውያን የሚዲያ ኣጋራችን ብለን በዚህ በትግል ወቅት የመሰረትነው ኢሳት መጨረሻው ይሄ ሆነ????ኢትዮጵያን ያፈራረሰና የራሱን ህዝብ በማንገላታት የሚታወቀው የአምባገነኑ የኢሳያስ ጤንነት የእኛ ጉዳይ ሆነ???ኢሳያስ ቀኑ ከደረሰ እንደወንጀል ተባባሪው የኛው የጣልያን ኣሽከር መለስ ዜናዊ ዛሬ ሳይሆን ለምን

ትላንት ወደሲኦሉ አይሰናበትም? ኣንድ ኣምባገነንግፈኛ ተወገደ ማለት ምናልባትም በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ህይወት ተረፈ ማለት እኮ ነው። እምነት ጥለንበት የነበረው ኢሳት ማንም ሳይልከው ኤርትራ ገብቶ የኢሳያስ ኣፈወርቂ ጡሩምባ ነፊ ሆነ? ምንድነው የሆነው? ኢሳያስ እንዴት ይህንን ያህል ታማኝ የሆኑ አሽከሮችን (ግንቦት ሰባትና ኢሳት) ማግኘት ቻለ? ኢሳት ወያኔን ከሚነቅፋባቸው ምክንያቶች ዋነኛው ያለምክንያት ጋዜጠኞችን ማሰሩና ተቃዋሚዎቹን በኣሰቃቂ ሁኔታ በማስገዱ ነው። ሌላው ኢሳትና ብርሃኑ ነጋ ወያኔን የሚነቅፉበት ጉዳይ ደግሞ የወያኔ ጭቆና የኢትዮጵያን ህዝብ ለስደትና ለኣደጋ ኣጋልጦኣል የሚል ነው። ታዲያ ምነው እንደወያኔ ኣምባገነን የሆነውን በሃገሩ ላይ ያሉትን ተቃዋሚ ጋዜጠኞች ለኣመታት እስርና እንግለት የዳረገውንና ህዝቡንም እንዲሰደድ ምክንያት የሆነውን ኢሳያስ ኣፈወርቂን ሊያነግሱት መረጡ?? ትንሽ እንኳዋን ምንተእፍረት የላቸውም? ዳያስፖራው ይህንን ኣለመጠየቁን ምን እንበል? አዚም???

መሳይ በኣሜሪካ እየዞረ ይዞ ያመጣውን የኢሳያስ ኣፈወርቂንና የተዋጊዎቹን ምስል ሲያሳይና ጥያቄ ሲመልስ ስለኣንድ ነፍሰ ገዳይ የኢሳያስ አፈወርቂ ጦር መኮንን ምሳሌ ወስዶ ሲናገር እንዲህ አለ (ቀጥተኛ ኮቴሽን ኣይደለም)። አንድ በነፍስ ገዳይነት የሚታማ የኢሳያስ ኣፈወርቂ ጦር መኮንንን ጋር በረሃ ውስጥ ተገናኝተን በጉዞ የተጎሳቆሉትን እግሮቼን ሊያጥብልኝ ጎንበስ አለ ካለ በሁዋላ ያ ትልቅ የጦር መኮንን ያንን ማድረጉ ልቡን እንደነካውና የጦር መኮንኑ ምን ያህል ትሁት ሰው ሆኖ እንዳገኘው በኣድናቆት ተናግሮ ያ ሰው እንኩዋንስ ነፍስ ሊያጠፋ ቀርቶ በሰው ላይ ክፉ የሚያስብ እንኩዋን አይመስለም ብሎ ኣረፈው። እኔ ያንን ስሰማ ከመገረምም አልፌ ትልቅ ጥያቄ ውስጥ ነበር የገባሁት። ለመሆኑ መሳይ መኮንን ት/ቤት አልሄደም እንዴ?? አቦጊዳ ሄውዞ በጉዲሃ ቄዝዦ ኣላለም እንዴ የኔታ ጋ ? ያ የኢሳይስ የጦር መኮንን ካሜራ ደግኖ ከኣሜሪካ ድረስ የመጣ ጋዜጠኛ ፊት ምን ኣይነት ባህሪይ እንዲያሳይ ነበር መሳይ የጠበቀው? መሳይ ይህንን ሳያውቅ ቀርቶ ነው ወይስ የዳያስፖራውን የመረዳት አቅም ከመናቁ የተነሳ ያንን የማይረባ ወሬውን ያምናሉ ብሎ ነው?

ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ኮስተር ብሎ መጠየቅ ያለበት ጥያቄ ቢኖር የኢሳትና የግንቦት ሰባት ፓርቲ ከ ኢሳያስ ኣፈወርቂ ጋር ያደረጉት ስምምነት ምን ላይ እንደተመሰረተ ነው። ጥያቄው ስምምነት ይኑራቸው ወይም አይኑራቸው ሳይሆን ይልቁንስ ያላቸው ስምምነት ምንን ያካተተ ነው የሚለው መሆን ኣለበት። ወድ ወገኖቼ ኢሳትና ግንቦት ሰባት እንዲህ ከኢሳያስ ኣፈወርቂ ጋር የተሞዳሞዱበት ጉዳይ እንቅልፍ ነስቶኛል። ኣንዱ ፍራቻዬ የወደፊቱዋን ነፃ ኢትዮጵያን ጥቅም ለኢሳያስ ለመስጠት ወይም ለማካፈል ኣስቀድመው የፈረሙት ስምምነት እንዳይኖር ነው። ከምጠረጥራቸው ጥርጣሬዎች ኣንዱ ምናልባት ኢሳያስ ኣፈወርቂ ኢሳትንና ግንቦት ሰባትን በገንዘብ ይደግፋቸው ይሆናል ብዬ ነው። ይህ የግል ግምቴ ነው። ለነገሩ ኢሳት የውስጥ

አሰራሩን መሸሸግ ልማዱ ነው። ግልፅነት የጎደለው መዋቅር ስለሆነ ነው ብዙ ጥርጣሬ ውስጥ የገባሁት ።

እንግዲህ የኢሳት ጋዜጠኞች ኤርትራ ሄደው ከተመለሱ በሁዋላ የተጠመዱበት ስራ ያው የገንዘብ ማሰባሰቡ ጉዳይ ነው። አሜሪካንን ካሰሱ በሁዋላ ወደአውሮፓ ሄደው ገንዘብ መልቀማቸውን ይያያዙታል። ስለገንዘብ ማሰባሰብ ካነሳሁ እላይ በጨረፍታ እንደጠቀስኩት ኢሳት የመላ ዳያስፖራውን ገንዘብ ለራሱ ብቻ እንጅ ለታጋዮች ትጥቅና ስንቅ እንደማያውለው ግልፅ ነው።። እንዲያው ባለፈው አመት አካባቢ ለትህዴን ይሁን ለግንቦት ሰባት ግንባሮች ገንዘብ ማሰባሰብ ሞካክሮ እንደነበር ትዝ ይለኛል። ለነገሩ ትሕዴንም ሆኑ ግንቦት ሰባት እዛው ኤርትራ በረሃ ውስጥ ቀልጠው እንዲቀሩ ኢሳያስ ማስተር ፕላን እንዳለው እኔ አልጠራጠርም። ኢሳይስ አፈወርቂ በስልጣን እያለ ማንም ተቃዋሚ ግንባር ከኤርትራ ወያኔን አይመታም። ምንም ቢሆን ከአማራውና ከኦሮሞው ይልቅ ለኢሳያስ ትግሬው ቀረቤታ አለው።ይህንን ነው ብርሃኑ ነጋና ኢሳት ሳይረዱ የቀሩት ወይም እያወቁ ለግል አጀንዳና ጊዜያዊ ጥቅም ሲሉ እንደማያቁ የሆኑት።

ሌላው የገረመኝ ደግሞ የወያኔ ሳያንሰን ትሕዴን የተባለው የትግሬዎች ግሩፕ ኢትዮጵያንን ከወያኔ እጅ ነፃ አዋጣለሁ እያለ በኢሳት መድረክ ላይ ስፍራ ተሰጥቶት መፋነኑ ነው። ቲፒ ኤል ኤፍ ከደርግ ነፃ አወጣችሁዋለሁ ብሎ (TPLF)ህዝቡን እንዳታለለ ማለት ነው (ኣንባቢ እዚህ ጋ ከት ብሎ የመሳቅ መብት አለው)።ጥያቄው ደግሞ ኢሳትና ግንቦት ሰባት ኣሁንም የዚሁ ምንነቱ ያልታቀ የትግሬዎች ተዋጊ ግንባር ዋና አሽቃባጭ መሆናቸው ምን የሚያውቁት ነገር ቢኖር ነው? ደግሞስ ትህዴን በምን ምክንያት ነው በየሳምንቱ በኢሳት ፕሮግራም ላይ ጊዜ ያገኘው?! ይህ ጥያቄ በተለይ የግንቦት ሰባትና የኣርበኞች ግንባር በኢሳት ያላገኙትን ፕሮግራም ትህዴን ብቻ ማግኘቱን ስናጤንበት የበለጠ ጥልቀት ያለው ይሆናል። ምክንያቱም ለትህዴን ፕሮፖጋንዳውን ጊዜ እንዲሰጥ ኢሳትን ወይ በገንዘብ ኣለበለዛም በእጅ ጠምዛዥነት ያስገደደው ሃይል ኣለ ማለት ነው። በገንዘብ ካልን ደግሞ የገንዘቡ ምንጭ ማ ሊሆን ይችላል ወደሚለው ጥያቄ ይወስደናል። ኢሳያስ አፈወርቂ? 90 በሙቶ። ይህ ብቻ ኣይደለም ትህዴን በኢሳት ፕሮግራም ከመያዙ በፊትም ከኤርትራ ምድር የሚያስተላለፈው የራሱ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ነበረው። ያንን ሁሉ በገንዘብ የሚሸፍነው ማን ይሆን? ይህ ሁሉ የኢሳያስ መሰሪው እጅ እንዳለበት ይሰማኛል ነገር ግን በተጨባጭ እስከማውቅ ድረስ በጥርጣሬ ሰነድ ላስቀምጠው። ጋዜጠኛ መሳይ መኮንን የኤርትራውን ቪዲዮ በኣንድ ስፍራ ለ ዳያስፖራው ሲያሳይ የትሕዴን ግንባር የራሱን ባንዲራ ከአክሱም ሃውልት ምልክት ጋር ሲያውለበልብ ኣይቶ የከነከነው ታዳሚ ተገቢ ጥያቄ ጠየቀ። “ለምንድነው ትህዴን ልዩ ባንዲራ ይዞ የሚታየው”? ወንድማችን መሳይ ለጥያቄው የሰጠው መልስ አንኳዋንስ ለኣዋቂ ለልጅም የማያጠግብ ነበር። “የራሳቸውን ባንዲራ የያዙት ኣርማቸው ስለሆነ ነው እንጅ በኢትዮጵያ የቀድሞ ባንዲራ ነው የሚያምኑት” አለ። በኢትዮጵያ ኣንድነት የሚያምኑ

ከሆነ የራስ አርማ ብሎ ነገር ኣለ እንዴ? ደግሞስ ስማቸውንስ የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ትህዴን) ብሎ ራሱን መጥራቱስ ጥያቄ ምልክት አይፈጥርም ወይ? እንዴታ። ትሕዴን ነገረ ስራው ለትግራይ መገንጠል የተዘጋጀ ኣካል እንደሆነ ነው እንጅ ለኢትዮጵያ ኣንድነት የሚሙዋገት ጎን ኣይታይበትም። በነገራችን ላይ የትህዴን ባንዲራና የወያኔ አርማ ተመሳሳይነት አለው (አክሱም ሃውልቱን መሃሉ ላይ)። ትህዴን ምኑም አይታመንም። አንዴ ብታታልለኝ ተወቃሹ አንተ ነህ ሁለተኛ ደግመህ ብታታልለኝ ግን ወቀሳው ለእኔ ነው የሚለውን የፈረንጆች አባባል ትህዴን ህሊና ውስጥ አልታተመም መሰለኝ ሁለተኝ ሊይታልለን ይከጅለዋል። ሁለተኛ ያልኩበት ምክንያት የመጀመሪያውን በወያኔ የተፈፀመውን ሸንገላ በመቁጠር ነው። ቲ ፒ ኤል አፍ ከደርግ ነፅ ኣወጣችሁዋለሁ በሚል ማታለያ ከደደቢት እምዬ ሚኒሊክ ቤተመንግስት ድረስ ሰተት ብሎ ገባ። ያንን ሳንወጣው ትሕዴን ደግሞ የራሱን ባንዲራ እያውለበለ ከወያኔ ነፃ አወጣችሁዋለሁ እያለ ሊሸጠን የመቃጣቱ ድፍረት አጅጉን ይገርማል። ምን ያድርግ ኢሳትና ግንቦት ሰባት ጆሮኣቸውን ሰጥተውታል በእነሱ በኩል የኢትዮጵያን ህዝብ ሊያሞኝ መንገድ ኣግኝቶኣል ቶሎ ካልነቃንበት።

ለመሆኑ ኤርትራ የሰፈሩት ተቃዋሚ ግንባሮች በከማል ገልቹ የሚመራውንም የኦሮሞውን ግንባር ጨምሮ ምነው ሲንቀሳቀሱ አይሰማም? ይህንን ያህል ታጋዮችን ኣሰልጥነው አስመረቁ እያለ የእነሱ ቱልቱላ ነፊ ኢሳት ኣለፍ ኣለፍ እያለ ይተርክልናል። በተለይ የኦሮሞው ግንባር ጭምጭምታው እንኩዋን ከተሰማ ኣምታት ተቆጥረዋል። ምነካቸው? ምን ዋጣቸው? ምናልባት የቀድሞዎቹ የወያኔ ተቃዋሚ ሃይሎች በእነ ፕሮፌሰር ሙሴ ይመራ የነበረው ላይ ያደረገውን ሳቦትጅና አፈና ኣይነት ኢሳያስ በከማል ገልቹም ላይ ተጠቅሞ ይሆን?? ጥርጥር የለውም። በኢትዮጵያ ሰማይ ድረገፅ የወጣውን የግንቦት ሰባት ገንዘብና ኣስተዳደር ሹም የኣቶ ሺፈራው ሺታውን የኤርትራ ስቃይ ማየት በቂ ነው። አቶ ሺታው ሺፈራው ሃላፊነቱና ተጠያቂነቱ በኤርትራ ሰፍሮ ያለው የብርሃኑ ነጋ (ግንቦት ሰባት) ግንባር ቢሆንም በገንዘብ ኣወጣጥ ጉዳይ ጥያቄ በማቅረቡ ብቻ በኢሳያስ ወታደሮች ታስሮ ሲቀጠቀጥና ለወራት ኢሰባዊ በሆነ ሁኔታ ሲሰቃይ እንደከረመ ይናገራል። ግንቦት ሰባት ሺታው ሺፈራውን ከኤርትራውያኑ ውርጅብኝ ሊታደገው አልሞከረም ኣልቻለም። ምክንያቱም ኤርትራ የገቡ ተቃዋሚ ሃይላት ሁሉ በኤርትራው ኢሳያስ ቁጥጥር ውስጥ በመሆናቸው ነው። ኢሳያስ ሲፈቅድ ይንቀሳቀሳሉ፣ ኢሳያስ ሳይፈቅድ በራሳቸው ፕሮግራም ምንም እርምጃ መውሰድ አይችሉም። እንግዲህ ኢሳቶችና ግምቦት ሰባቶች የሚነግሩን ኢትዮጵያ ነፃ የምትወጣው በኢሳያስ ቁጥጥር ባሉቱ ተዋጊዎች ነው ማለት ነው። ይህ “ድንቄም” የሚያሰኝ ነው። ባጭሩ ኤርትራ ውስጥ ያሉቱ ተቃዋሚ ግንባሮች እጣቸው እዛው ኤርትራ በረሃ ውስጥ ሰፍረው ኢሳያስን ከመንግስት ገልባጮች እየጥበቁ ከመኖር በተቀር ለትዮጵያ የነፃነት ፍልሚያና ትግል ኣስተዋፅኦ ያደርጋሉ ብዬ በውን ቀርቶ በህልሜም አላስብም። በቅርቡ የግንቦት ሰባትና የኣርበኞች ግንባር ተቀላቀሉ ከተባለስ በሁዋላ የሆነውን ሰምተን ይሆን? ጥያቄው እኮ ለምንድነው ግንቦት ሰባትና ኢሳት ኤርትራ ካልገባን በተቀር ከሌላ ስፍራ ወያኔን መዋጋት አይቻልም የሚሉን? ቲ ፒ ኤል

ኤፍ የት ሆኖ ነው ደርግን ኣስራ ሰባት አመት የወጋው? በሁዋላም ድል ያደረገው? ነው ወይስ ወያኔ የሃገሪቱን አያንዳንዱዋን ካሬሜትር ይቆጣጠራል ነው የሚሉን? ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ ሽምቅ ውጊያ ማካሄድ ከመቻሉም በላይ ኤርትራ ውስጥ ከመወዘፍና የኢሳያስን ፍቃድ እየጠየቁ ከመንቀሳቀስ ይልቅ እጅግ ውጤታማው ያ ነው።

በኣሁኑ ወቅት ኢሳትና ግንቦት ሰባት የዳያስፖራውን የትግል ትኩረት አናግተውታል። የኢሳያስና የኤርትራ ኣሽከሮች ሆነው የኢትዮጵያንም ህዝብ ኣብሮኣቸው ገሌ እንዲገባ እየወተወቱት ነው። ውሻ በበላበት ይጮሃል እንዲሉ ኢሳትና ግንቦት ሰባት ከኢሳያስ ጉዋዳ የሚሰፈርላቸው ቀለብ እንዳለ አይነት ለአምባገነኑ ከበሮ መቺ ሆነዋል። ይ ደግሞ ሊያስቆጣንና ሊቀሰቅሰን ይገባል። እስከመቼ ድረስ የማንም መጨዋቻ እንሆናለን ጎበዝ?

## ምን ማድረግ አለብን?

1/ ያለማመንታት የትጥቅ ትግሉ የሚጠነሰስበትንና የሚጀመርበትን መንገድ መቀየስ። የኢትዮጵያ ህዝብ ዳያስፖራውን ጨምሮ በሃገሪቱዋ ምድር ላይ የሰፈሩ ተዋጊ ግንባሮች ሊኖረው ያንንም ኣካል በገንዘብና በስትራቴጂ ሊደግፍ ይገባል። ማንነታቸው በደንብ የተጠናና የሚታመኑ ተዋጊ ግንባሮች በኢትዮጵያ ምድር ቢኖሩና ከዳያስፖራውም ሆነ በሃገር ውስጥ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እነኝህን ግንባሮችህ ሊቀላቀሉ የሚፈልጉ ቢኖሩ ለእነሱ የሚስጥር መንገድ ማመቻቸት ተቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል።

2/ ኤርትራንና የኤርትራውን መሪ ኢሳያስን በትግላችን ውስጥ ፈፅሞ አለማስገባት። ኢሳያስ በኢትዮጵያ ላይ ያለው ኣቁዋም በሃያ አመት ኣይደለም በአርባም አመት አይቀየርም። ኤርትራን የገነጠለው ጊዜ ያልቀየረው የዘመናት ቂምና ቁርሾ ይዞ እንደነበር ማስታወስ ያስፈልጋል። እንግዲያውማ ኤርትራውያኖች በሃይለስላሴም ሆነ በደርግ ዘመን በሃገሪቱዋ ላይ የተሻለ ኑሮ የነበራቸው ኣልነበሩም እንዴ? ምነው ያ የቆየ ቂማቸውን ኣላስቀየራቸውምና ኢትዮጵያን እናት ሃገራችን ብለው ኣልተቀበሉም? ያንን ካነሳን ደግሞ ትግሬዎችስ ቢሆኑ ከኣማራውና ከሌሎችም ጎሳዎች ይልቅ በትላልቅ ደሞዝ ተቀጥረው የሚሰሩ ትላልቅ ቢዝነስ የነበራቸው ኣልነበሩም እንዴ ባለፉት መንግስታት? ምነው ዛሬ ኢትዮጵያን ኣንቅረው ተፉዋት? ታሪኩዋን ሊደልዙና ሊያጠፉ ተነሱ? ኤርትራውያኖችና ትግሬዎች ከበጣም ጥቂቶች በተቀር ከኢትዮጵውያን ጋር ሊታረቅ የማይችል ኣጀንዳ አላቸው። ኣመታትም አይቀይሩትም። ስለዚህ ኢሳያስ ዛሬ ተለውጦኣል፤ ዛሬ የኢትዮጵያ ወዳጅ ሆኖኣል የሚሉ ቢኖሩ የመጨረሻ ነሆለሎች ናቸው። ኢሳያስ የሚያደርገውን ያውቃል። እንደብርሃኑ ነጋ ኣይነት ሃሁ ቆጥረናል የሚሉ ሰዎች የጎረሱት ጉርሻ ከሌላቸው በተቀር ኢሳያስ

የሚታመን ነው ብለው አስይሰብኩንም ነበር። አንዳርጋቸው ፅጌም እንዲሁ። ኤርትራውያኖችና ትግሬዎች ኢትዮጵያን እንደኩዋስ እየተቀባብሉ ይጫወቱባታል። ትህዴንና ኢሳያስ ከወያኔ ሊቀበሉዋትና እነሱ ደግሞ ለተወሰኑ አመታት ጢብጢብ ሊጫወቱባት ነውና ኢሳትንና ግንቦት ሰባትን ካሉበት ቅዠት እንዲወጡ አለበለዛም ለዘለአለም ወደጥልቁና ወደፅልመቱ እንዲገቡ ማስገደድ ግድ ይሏል።

3/ ኢሳትን በጭፍን ማመን ያብቃ። ኢሳት ባለቤቱ ማነው ኣቁዋሙስ ምንድ ነው? ከኢሳያስ ጋር ያለው ግንኙነት ይዘቱ ምንድ ነው? ምንንስ ያካትታል? በኢሳት በግንቦት ሰባትና በኢሳያስ መሃከል የተፈፀመ ድብቅ ስምምነት አለ ወይ? ይህን የኢትዮጵያ ህዝብ ማወቅ መብቱ ነው። ይህንን መጠየቅ ያስፈልጋል።

4/ ኢሳት የኢትዮጵያን የኤርትራን ህዝብ ኣስታራቂ አድርጎ የመረጠው ወይም የላከው ማንም የለም። የሰሞኑ አስታራቂነት ኣጀንዳው ምንድ ነው? ኤርትራ ኢትዮጵያን አልፈልጋትም ብላ የሄደች እሱዋ ናት። የዛሬው ወሬ ከየት የመጣ ነው?። እላይ እንደጠቀስኩት መቼም የኢሳያስም ሆነ የኤርትራውያኑ በኢትዮጵያ ላይ ያላቸው አቋዋም መቼም አይቀየርም። በአጥንትና በደም ውስጥ የተቀበረ የትውልድ ቅራኔ ነው። እርግጥ ይህንን ስል ጠላታሞች ነን ማለቴ ኣይደለም ነገር ግን የሰሞኑን እፍ እፍ ምን ይሉታል? ከበስተሁዋላው የሆነ አጀንዳ አለ ግድ የላችሁም።

5/ ዳያስፖራው ከኢሳት ሌላ ኣማራጭ ሚዲያ ያስፈልገዋል። የኢትዮጵያን ህዝብ በፕሮፖጋንዳና በአጂቴሽን (Agipropoganda) ለትግል የሚያዘጋጅና የሚያንቀሳቅስ ጠንካራ አቋዋም ያለው መገናኛ ያስፈልጋል። ዳያስፖራው በዚህ ዙሪያ ውይይት መጀመር ያስፈልገዋል።

6/ ዳያስፖራው ለኢሳት የሚሰጠውን ድጋፍ ቆም ብሎ መመርመር ይገባዋል። ኢሳት ኤርትራ ገብቶአል። ያም ስለሆነ ኢሳያስ ይደግፈው። የግንቦት ሰባትም አባላት ቆም ብለው ማጤን ኣለባቸው። ግንቦት ሰባትም ኤርትራ ገብቶኣል የኢትዮጵያ ኢጋር የመሆን እድሉ አሁን ዜሮ ነው። ምነው ታጋዮችን እናስታጥቅ፣ ትጥቅና ስንቅ እንላክ፣ ገንዘብ እንሰብስብ? የሚል እንቅስቃሴ ከታማኝና ከኢሳት አይሰማም? ሁልጊዜ ለኢሳት ነው ሩጫው። ኢሳት ነፃ ያወጣን ይመስል? ጉልበትንና ገንዘብን ለግንቦት 7 ማጥፋት ኪሳራ ነው። ኢሳትም ሆነ ግንቦት ሰባት ከኤርትራው ኢሳያስ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እስካላቆሙና አግራቸውን ከኤርትራ እስካላወጡ ድረስ ዳያስፖራው ጆሮውን ሊሰጣቸው ኣይገባም።

ወያኔ ይብቃው
ኢትዮጵያችን ጠላቶችዋን እንደገና ታሳፍራለች።